የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሳኛ ዓመት ቁጥር ፵፮
አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No. 46
ADDIS ABABA, 19th July, 2024

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፲፭/፪ሺ፲፮

ለኢትዮጵያ የዲጂታል መታወቂያ ለአካታችነትና አገልግሎት አሰጣጥ ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ…………………………………...…ገጽ ፲፭ሺ፯፻፲፯

## Content

Proclamation No. 1315/2024

International Development Association Loan Agreement for Financing Ethiopia Digital ID for Inclusion and Services Project Ratification Proclamation………...……..…... Page15717

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፲፭/፪ሺ፲፮

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ**

ለኢትዮጵያ የዲጂታል መታወቂያ ለአካታችነትና አገልግሎት አሰጣጥ ማስፈጸሚያ የሚውል ኤስ.ዲ.አር ፪፻፳፰ ሚሊዮን ፪፻ሺ (ሁለት መቶ ሀያ ስምንት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር) ብድር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ታህሳስ ፲፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

## Proclamation No. 1315/2024

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION**

**WHEREAS**, the Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association shall provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan an amount equivalent to SDR 228,200,000 (Two Hundred and Twenty-Eight Million Two Hundred Thousand) Special Drawing Rights for Financing Ethiopia Digital ID for Inclusion and Services Project, was signed in Addis Ababa on 21st day of December, 2023;

ይህን ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፭ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም በአካሄደው ፲፯ኛ መደበኛ ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለኢትዮጵያ የዲጂታል መታወቂያ ለአካታችነትና አገልግሎት አሰጣጥ ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፲፭/፪ሺ፲፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ታህሳስ ፲፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 7463-ET በዚህ አዋጅ ጸድቋል፡፡

**፫. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ኤስ.ዲ.አር ፪፻፳፰ ሚሊዮን ፪፻ ሺ. (ሁለት መቶ ሀያ ስምንት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺ. ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**WHEREAS**, the House of Peoples' Representatives of the Federal Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 14th day of March 2024;

**NOW, THERFORE**, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby Proclaimed as follows.

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Loan Agreement for Financing Ethiopia Digital ID for Inclusion and Services Project Ratification Proclamation No. 1315/2024".

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement Number 7463-ET signed in Addis Ababa on 21st day of December, 2023 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

**3. <u>Power of The Ministry of Finance</u>**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan an amount equivalent to SDR 228,200,000 (Two Hundred and Twenty-Eight Million Two Hundred Thousand SDR ) Special Drawing Rights in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

## ፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፪ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም**

**አብይ አህመድ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 19th Day of July,2024**

**ABIY AHMED (Dr.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**